# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ተዛማጅ ሠነዶች፦ COA, COA-RA, COB-RA, IOI-RA, JFA, JGA, JGA-RB, JGA-RC, JHC, JHC-RA
ኃላፊነት የሚመለከተው ቢሮ፦ Office of School Support and Well-being

## የተማሪን ባህሪ ለማቅናት የሚደረግ ጣልቃገብነት

I. **አላማ**

ደህንነቱ የተጠበቀ ሠላማዊ የትምህርት አካባቢን ለመጠበቅ የተማሪን ባህርይ የማቅናት ጣልቃገብነትን ቀጣይነት በሚመለከት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቅደምተከተል ሥርአት ለመዘርጋት ነው።

II. **ዳራ**

ለአካደሚያዊ ስኬት የሚመች አወንታዊ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እንዲቻል የተማሪን ስነምግባር ለመምራት ተቀዳሚ ሃላፊነት የሚመለከተው የትምህርት ክፍል መምህርን ነው። የአወንታዊ ባህርይ ጣልቃ ገብነትን መጠቀም አስቸጋሪ ባህርይን ከመከላከል ወይም ከመቀነስ ባሻገር አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ-ስሜታዊ እድገትን ያዳብራል። በመረጃ-የተደገፈ፣አካላዊ ጉዳትን የማያስከትሉ ድርጊቶች፣ ማስተማር፣ እና ተገቢ የሆነ ኃላፊነት የተሞላበት፣ የተማሪን ባህሪ የማቅናት ስልት/ስትራቴጂ ያለው እና ውጤታማ የትምህርት አውድ ያመቻቻል።

ሰራተኞች የተማሪን ባህሪ ለማቅናት እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሠላም የሰፈነበት የትምህርት አካባቢን ለመጠበቅ ብዙ አይነት አወንታዊ-የጣልቃ ገብነት ስልቶችን እና ድጋፎችን ይጠቀማሉ።

ሰራተኞች ማግለልን ወይም የአካል ማገጃ ስልት መጠቀም ያለባቸው ሌላ የተቻለ አማራጭ ጥረት ሁሉ ከተደረገ በኋላ ብቻ ነው –

A. ቀጣይነት ያለው አወንታዊ፣ አነስተኛ የአካል መገደብ ወይም አማራጭ ጥረቶች ተሞክረው ካልተሳኩ ወይም በተገቢ ሁኔታ ደህንነቱ የተጠበቀ አወንታዊ የትምህርት አካባቢን ለማስጠበቅ እንዳልተቻለ ከተረጋገጠ በኋላ፣

B. አካልን ማገድ ከሚያስከትለው ስጋት ይልቅ የባህርይ ሁኔታ የሚያስከትለው ጉዳት የሚበልጥ ከሆነ፣

C. ከስቴት ደንቦች ጋር ወጥነት ባለው መልክ በርህራሄ፣ ጉዳት የማያስከትል፣ እና የተሻለ ውጤት በሚሰጥ አኳኋን፣

D. ለመጉዳት ወይም ምቾት ለመንሣት እንዳይሆን፣ ከስቴት ደንቦች ጋር ወጥነት ያለው ተግባር፣ እና

E. ተማሪው(ዋ) ካለበ(ባ)ት የታወቀ የጤና/የህክምና ወይም የስነልቦና ውስንነቶች እና የተማሪው(ዋ)ን ባህርይ የማቅናት ጣልቃገብነት እቅድ (BIP) ወይም በግላዊ ሁኔታ ተመርኩዞ የተዘጋጀ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

III. **ትርጉም**

A. BIP የተማሪን አስቸጋሪ ባህርይ ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ እና ተገቢነት ያለው ባህርይ ማጎልበትን ለመደገፍ በተግባራዊ የባህሪ ግምገማ (FBA) ላይ በመመስረት የሚዘጋጅ በመረጃ ላይ የተመሰረተና የተዋቀረ የቅድመ ጥንቃቄ እቅድ ነው።

B. ግንኙነትማለት በቃል ንግግር ወይም ያለንግግር መረጃ ማስተላለፍ ነው። "ግንኙነት" ማለት በዚህ ብቻ ባይወሰንም –

1. በንግግር፣

2. በሰውነት እንቅስቃሴ ፍላጎትን መግለጽ፣

3. በምልክቶች፣ እና

4. በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ ሃሳብን/ፍላጎትን መግለፅ ነው።

C. ኮንፈረንስ ማለት፡- በሠራተኞች፣ በወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና/ወይም በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው።

D. ተካታታይነት ያለው የተማሪን ባህርይ ለማቅናት የሚደረጉ በቅደምተከተል የተቀመጡ ጣልቃገብነቶችከሞንጎመሪ ካዉንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ የስነምግባር ኮድ MCPSጋር የሚጣጣም ተገቢ ድጋፎችን ከማድረግ ጀምሮ የተማሪን ባህርይ ለማቅናት በቅደምተከተል የሚከናወኑ ስልታዊ ተግባሮች ናቸው።

E. አካላዊ ቅጣትየተከለከለ ሲሆን፣ ሃላፊ በሆነ(ች) ሰው አማካይነት ሆን ተብሎ በአካል ላይ በሚደረግ ቅጣት ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ነው።

F. ማግለል ማለት፡- ተማሪው(ዋ) ልዩ ትምህርትን ጨምሮ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ወይም ድጋፍ በማይሰጥበት ሁኔታ በማግለል ራሱ(ሷ)ን እንዲገዛ/እንድትገዛ ለማድረግ ለተወሰነ ጊዜ ክትትል በሚደረግበት ቦታ እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ ነው።

G. FBA ማለት፡- አስቸጋሪ ባህርይን ለማቅናት ወይም ለማሻሻል ውጤታማ እና ስኬታማ የሆነ BIP ለማዳበር መረጃ የሚሰበሰብበት የስልታዊ ዘዴ መመሪያ ነው። FBA የሚከተሉትን ያጠቃልላል –

1. የተማሪ አስቸጋሪ ባህርይ ድርጊቶችን ለይቶ ማወቅ፣

2. በትምህርት አውድ ላይ የሚታይ የባህርይን ችግር መግለጽ፣ እና

3. ወደፊት የሚከሰቱ ወይም የማይከሰቱ፣እና ባህርይን ለማቅናት የሚታሰቡ አካባቢያዊ እና ሌሎች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ወይም ለመተለም የሚረዱ ምክንያቶችን እና ሥፍራዎችን ለይቶ ማወቅ።

H. በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረግ ባህርይ የማቅናት ጣልቃ ገብነት (ISI) ለተወሰነ ጊዜ ተማሪን ከትምህርት ክፍል ማስወጣት ነው። ISI እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ፥ ተማሪው(ዋ) የሚከተለው እድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል –

1. አጠቃላይ ስርዓተ-ትምህርቱን በአግባቡ የመቀጠል፣

2. COMAR 13A.05.01 ድንጋጌ መሰረት ተማሪው(ዋ) የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ከሆነ(ች) በተማሪው(ዋ) IEP ውስጥ የተጠቀሱትን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማግኘት፣

3. ተማሪው(ዋ) በመደበኛ የትምህርት ክፍል ከሚሰጠው ፕሮግራም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ማግኘት፤ እና

4. ተገቢ እስከሆነ ድረስ በወቅቱ እኩዮቹ(ቿ) በሚያደርጉት የትምህርት ፕሮግራም ላይ መሳተፍ።

I. የጤና እንክብካቤ ድርጅቶች እውቅና የጋራ ኮሚሽን (የጋራ ኮሚሽን) በዩናይትድ ስቴትስ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን እና ፕሮግራሞችን እውቅና የሚሰጥ እና የሚያረጋግጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። በአገር-አቀፍ ደረጃ የአንድ ድርጅትን ግዴታ የተወሰኑ የአፈፃፀም መመዘኛዎችን ለማሟላት የሚንፀባረቅ የጥራት መለያ አርማ በመሆን የሚታወቅ ነው።

J. አዎንታዊ የባህሪ ጣልቃገብነቶች፣ ስልቶች እና ድጋፎች ማለት፡- አስቸጋሪ እና ፈታኝ የባህርይ ድርጊቶችን በመከላከል ወይም በመቀነስ አወንታዊ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገትን ለማበረታታት በትምህርት ቤት እና በግለሰባዊ መረጃ ላይ የተደገፉ ድርጊቶችን፣ መመሪያዎችን እና እገዛን በመጠቀም ትምህርታዊ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ስኬትን ለማበረታታት የሚደረግ ጥረት ነው።

K. መከላከያ ወይም ማረጋጊያ መሳሪያ ማለት፡- ከተማሪው(ዋ) አካል ጋር የሚያያዝ መሳሪያ ወይም ቁሳቁስ ሲሆን የመንቀሳቀስ ነፃነትን የሚገድብ ወይም ለተማሪው(ዋ) የአካል ክፍል የእንቅስቃሴ መዳረሻን የሚገድብ በተግባር ራስን የመጉዳት ባህሪን ለመከላከል፣ ወይም የአንድን ሰው አስተማማኝ አቀማመጥ ለመጠበቅ የሚጠቅም ማገጃ ነው። የመከላከል፣ ወይም የማረጋጋት ማገጃ መሣሪያ የሚያካትተው–

1. አምራች ድርጅቱ መሣሪያውን ለሠራበት ዓላማ መጠቀሚያ የሚውል ከሆነ፣ በጤና ባለሙያ የታዘዘ እና እንደአስፈላጊነቱ ማስተካከል የሚቻል መሳሪያ ሆኖ፣

2. የመቀመጫ ቀበቶ፤ ወይም

3. በህዝብ የትራንስፖርት ኤጀንሲ እቅድ መሰረት ተማሪዎችን በሚጓጓዙበት ጊዜ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚረዱ ሌሎች መሳሪያዎች

L. ማገጃ – የታሰበው የአካል እንቅስቃሴ መገደቢያ አጠቃቀሙ የሚፈቀድ መሆኑን ይረጋገጣል።

1. ትምህርት ቤቱ የጋራ ኮሚሽኑን መስፈርት በማሟላት ካልተፈቀደለት በስተቀር፣ በማንኛውም የህዝብ ወይም ህዝባዊ ያልሆነ ት/ቤት በማሽን እንቅስቃሴን ማገድ የተከለከለ ሲሆን፣ ይኼውም፡- ማንኛውንም የአካል እንቅስቃሴን የሚገድብ መሣሪያ ወይም ቁሳቁስ በመጠቀም የተማሪን የመንቀሳቀስ ነፃነት ወይም ማንኛውንም የሰውነት ክፍል መገደብ እና ተማሪ በቀላሉ ማስወገድ የማይችል-የማትችል አይነት የእንቅስቃሴ መሣሪያ መጠቀም ማለት ነው። ሜካኒካል የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ በሰለጠነ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በተማሪ አማካኝነት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመከላከያ ወይም የማረጋጊያ መሳሪያዎችን የማያካትት ሲሆን፣ በተገቢው የህክምና ባለሙያ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት በሚሰጥ ባለሙያ የታዘዙ እና እንደነዚህ ያሉ መሳሪያዎች ለተዘጋጁት ልዩ እና የተፈቀዱ አላማዎች ብቻ ጥቅም ላይ ይውላሉ–

a) ተገቢውን የአካላዊ እንቅስቃሴ ሚዛን ለማስጠበቅ፣ወይም የተሻለ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲረዳ እና ያለመሣሪያ ድጋፍ እንደልብ ለመንቀሳቀስ የማያስችል ከሆነ እንዳስፈላጊነቱ ሰውነት ላይ ተገጥመው መጠቀሚያ የሆኑ መሣሪያዎች ወይም ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች ይሆናሉ -adaptive devices or mechanical supports፡-

b) በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪ-ተማሪን ለማጓጓዝ በታቀደ ዓላማ የተማሪን ደህንነት ለመጠበቅ ጥቅም ላይ የሚውል የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ፣

c) በህክምና ምክንያት የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ፣ ወይም

d) ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች የተማሪን ተሳትፎ ለመደገፍ በአጥንት ህክምና ባለሙያ የታዘዙ መሣሪያዎች።

2. በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለጹት ሁኔታዎች ምክንያት ብቻ ተቀባይነት ያለው የአካልን እንቅስቃሴ መገደብ ፣ በሜሪላንድ ህግ የተማሪን የመንቀሳቀስ አቅምን የሚቀንስ ወይም የሚገድብ የግል እንቅስቃሴ መገደቢያ ተብሎ ይገለጻል። የሰውነት አካል፣ ክንዶች፣ እግሮች ወይም ጭንቅላት እንደፈለገው የመንቀሳቀስ ሁኔታን የሚገድብ ይሆናል። የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ የሚከተሉትን አያካትትም –

a) ተማሪን ለማረጋጋት ወይም ለማመቻቸት ለአጭር ጊዜ ያዝ ማድረግን፣

b) አካልን ማጀብ፣ ይህ ማለት ተማሪ ወደ ሠላማዊ ቦታ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ ካልሆነ/ች (ይህ ማለት፦ በአካል መሸኘት ረዥም ጊዜ የሚወስድ ካልሆነ እና የተማሪን በነፃነት የመንቀሳቀስ ሁኔታን የማይገድብ ከሆነ፣ ለማበረታታት ያህል በጊዜያዊነት እጅን፣ የእጅ አንጓ፣ ክንድ፣ ትከሻ፣ ወይም ጀርባን በመያዝ ጊዜያዊ አካላዊ እጀባ ማድረግ፣

c) ምክር መስጠት የመሣሰሉ ሌሎች ዘዴዎች የማይሰሩ ከሆነ በመረበሽ፣ በመበጥበጥ፣ በማወክ አካባቢን ለመልቀቅ ፈቃደኛ የማይሆን/የማትሆን ተማሪን ከአካባቢ ለማንቀሳቀስ፣

d) ድብድብ ውስጥ ጣልቃ መግባት/መገላገል።

3. በደረት አጋድሞ እንቅስቃሴን ማገድ/Prone restraints፣ በማንኛውም ህዝባዊም ሆነ ህዝባዊ ባልሆነ ት/ቤት የተከለከለ ሲሆን፣ተማሪው(ዋ) ወለል ላይ በደረቱ(ቷ) ተድፍቶ(ታ)፣የአካል እንቅስቃሴ እንዳይኖር የሚያግድ የእንቅስቃሴ ማገጃ ነው።

M. ማግለል ማለት፦

1. ተማሪ በአካል እንዳይ(ት)ሄድ በተከለከለ(ች)በት ክፍል ወይም አካባቢ ተማሪን ብቻው(ዋ)ን ማቆየት ማለት ነው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በማንኛውም ሁኔታ ማግለል የተከለከለ ነው።[1]

2. “ማግለል” ተማሪን ለብቻ ነጥሎ ማስቀመጥ አንዳንዴ ጊዜ (“time out”) የሚባለውን የተማሪን ባህሪ ማቅናት ጣልቃገብነት እቅድ አያካትትም –

a) ተማሪ መውጣት የሚችልበት/የምትችልበት ያልተቆለፈ ክፍል ውስጥ፣ ወይም

b) ክፍል ውስጥ ተማሪው(ዋ) በአካል እንዳይወጣ/እንዳትወጣ ያልተከለከለበት የተለየ ቦታ።

---

[1] የሜሪላንድ ህግ በማንኛውም የሜሪላንድ ህዝባዊ ኤጀንሲ አካላዊ ማግለልን ይከለክላል፤ የትምህርት ዲፓርትመንት (ትምህርት) የአካባቢ ትምህርት ቤት የታዳጊዎች ትምህርት አገልግሎት ፕሮግራም የሜሪላንድ መስማት የተሳናቸው ት/ቤት፣የሜሪላንድ ዓይነ ስውራን ትምህርት ቤት ወይም የወጣቶች ትምህርት አገልግሎት ፕሮግራም (An Code ED 7- 1101 (e))።

N. ማገድ አንድን ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከተማሪው(ዋ) መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ማግለል ነው፣ ይህም MCPS ደንብ JGA-RB፣ መታገድ እና መባረር፣ እና ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማገድ እና ማባረርሙሉ በሙሉ ተገልጿል።

O. በአስጨናቂ ገጠመኝ ምክንያት የሚፈጠረውን የጤንነትም ሆነ የስነ-ልቦና ቀውስ ትኩረት በመስጠት የሚደረግ ጣልቃ ገብነት፡- ማለት በረብሻ ምክንያት፣ በብዝበዛ፣ በቸልተኝነት/በግዴለሽነት፣ በከባድ ችግር ወይም ቀውስ ምክንያት፣ በረብሻ፣ እና በጦርነት፣ዳፋ ተማሪው(ዋ) ትምህርቱ(ቷ)ን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን እንዳይችል-እንዳትችል ያስከተለው አካላዊ እናስሜታዊ-ስነልቦናዊ ጉዳት፣ የጤና መቃወስን እና ችሎታን ያገናዘበ አቀራረብ ነው።

P. የስራ ቀን ማለት ከቅዳሜ፣ እሁድ፣ ወይም ሌላ ህጋዊ የበአል ቀን ውጪ የሆነ ቀን ነው፣ ሆኖም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማዕከላዊ ቢሮዎች ለስራ ክንውን ክፍት የሚሆኑባቸው ቀኖች ናቸው።

## IV. የአሠራር ቅደምተከተል

A. የክፍል አስተማሪ እና የተማሪ ግንኙነት ለተማሪ ስኬት እና ለት/ቤት ስኬት ወሳኝ ነው። አወንታዊ፣ ሰላማዊ፣ እና ስነ ስርአት የሰፈነበት የትምህርት አካባቢን መመስረት ሁሉም ተማሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸው ግልፅ፣ እና ከፍተኛ አካዴሚያዊና የስነምግባር መስፈርቶችን ማበጀት ነዉ።

B. ሰራተኞች ለሁሉም ተማሪዎች አካዳሚያዊ ስኬትን የሚደግፍ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ስርዓት ያለው የመማሪያ አካባቢ ለመፍጠር የተነደፉ ውጤታማ የክፍል አመራርና አያያዝ ስልቶችን ይጠቀማሉ።

C. በቦርድ ፖሊሲ JGA፣የባህሪ ማቅናት ጣልቃገብነት፣ደህንነት እና የደህንነት እቅድ፣ የተማሪ ባህሪ የማቅናት ጣልቃገብነት ስልቶች ተማሪዎችን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ በሆነ መልኩ በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራማቸው ውስጥ እንዲሳተፉ በሚያስችል መንገድ መተግበር አለባቸው። የትምህርት ቤት ሰራተኞች ግጭትን ለመከላከል እና አስፈላጊ ሲሆን ምላሽ ለመስጠት፣ የተማሪዎችን ልዩ ልዩ የባህሪ ፍላጎቶች ለማሟላት እና የባህሪ ማቅናት ጣልቃገብነት ፖሊሲዎችን እና ተግባራትን በፍትሃዊነት ለመተግበር የሚያስፈልጉትን ድጋፍ፣ እውቀት እና ክህሎት የተቀዳጁ ይሆናሉ።

D. በቦርድ ፖሊሲ COA መሠረት፥ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም፣ እያንዳንዱ ርእሰ መምህር ትምህርት ቤቱ ጠብ እና ረብሻ ደብድብ ሲነሳ ማብረድና ማስቆም፣በአካል-ጣልቃ ገብተው መገላገል፣ እንዲሁም የመተባበር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለማግባባት ስልጠና ያላቸው ሰራተኞች እንዳሉት የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።ያለመተባበር ችግርን መፍታት፣ መነሻ ምክንያቱን መተንተን፣ የአእምሮ ጤና ድጋፍ ለመስጠት፣ በትምህርት ላይ በትኩረት እንዲሳተፉ ድጋፍ የመስጠት ጣልቃገብነቶች፣ እና የማህበረሰብ መገልገያዎች/ሪሶርሶች መኖራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነቱ ይመለከተዋል/ይመለከታታል።

E. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ የስነምግባር ህግ ከተማሪ ባህሪ ጋር በተያያዙ ማህበራዊ፣አካዳሚክ እና ግላዊ ጉዳዮች ላይ መፍትሄ ማግኘት ሲያስፈልግ ተማሪዎችን እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ማሳተፍን ያበረታታል። የክፍል መምህሩ(ሯ) የተማሪው(ዋ) ባህሪ የርእሰመምህሩን/ተወካይ፣የካውንስለሩን፣የትምህርት ቤቱን የስነ-ልቦና ባለሙያ/ሳይኮሎጂስት፣የተማሪ ሰራተኛን፣ ወይም የልዩ ባለሙያን ትኩረት በሚፈልግበት ጊዜ ለርእሰ መምህሩ/ለተወካይ ያሳውቃል/ታሳውቃለች፤ እና በርእሰመምህሩ/ተወካዩ አማካይነት በተቻለ ፍጥነት ኮንፈረንስ ይዘጋጃል።

F. ማግለልን ወይም እገዳን ከመጠቀም በፊት፣የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው የአዎንታዊ ባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶችን እና ድጋፎችን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ጣልቃገብነቶች የተማሪው(ዋ) መብት በክብር እንዲጠበቅ እና ከመነሳቆል ነፃ የመሆንን መብት ማክበር ኣለባቸው።

G. ይህንን ደንብ እና የሜሪላንድን ህግ በማክበር ማገጃን ለመጠቀም የተመደቡ እና የሰለጠኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ብቻ ማገጃን እንደ የባህሪ-ጤና ጣልቃገብነት መጠቀም ይችላሉ።

1. ሌሎች ብዙም አካላዊ ያልሆኑ ጣልቃ ገብነቶች እንዳልተሳኩ ወይም ተማሪው(ዋ)ን ከጉዳት ለመከላከል አግባብ እንዳልሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ማገድ ተማሪው(ዋ)ን ወይም ሌላ ግለሰብን ከአይቀሬ ከባድ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ/ለመከላከል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ እንደ ባህሪ-ጤና ጣልቃገብነት ሊያገለግል ይችላል።

2. በምንም አይነት ሁኔታ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥነ ሥርአት ለማይታዘዙ ወይም ወይም የመተንኮስ ባህሪ ላላቸው ተማሪዎች አካልን የማገድ ተግባር እንዲጠቀሙ አይፈቀድም።

3. በሜሪላንድ ህግ እና MCPS ደንብ COB-RA መሠረት፣ የክስተት ሁኔታን ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ፣የ MCPS ሰራተኞች ረብሻን ለማስወገድ እና/ወይም ለመከላከል ምክንያታዊ እና አስፈላጊ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ።

V. **ማግለል፣ ለብቻ እንዲቆይ-እንድትቆይ ማድረግ**

A. የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪን ማግለል፣ለብቻ እንዲ(ድት)ሆን ማድረግን መጠቀም ያለባቸው የተማሪው(ዋ) ባህርይ –ከሆነ መፍትሔ ለመሻት

1. የተማሪው(ዋ) ባህርይ በተማሪው(ዋ) ትምህርት የመከታተል ሁኔታ ላይ ወይም በሌሎች የመማር ሁኔታ ላይ ተቀባይነት በሌለው ማደናቀፍ የሚያስቸግር ከሆነ፣

2. የተማሪው(ዋ) ባህሪ ድንገተኛ አደጋን የሚፈጥር እና ተማሪን ወይም ሌላ ሰውን ከሚደርስ ከባድ የአካል ጉዳት ለመከላከል አካላዊ ያልሆኑ ጣልቃገብነቶች ካልተሳኩ ወይም አግባብ እንዳልሆኑ ከተረጋገጠ ማግለል አስፈላጊ ነው።

3. ማግለል በተማሪው(ዋ) ከተጠየቀ፣ ወይም

4. በተማሪው(ዋ) BIP ማግለል የሚደገፍ ከሆነ።

B. የማግለል ተግባር በተማሪ አቅምና ችሎታ (የማወቅ (ኮግኒቲቭ)፣ ማህበራዊ ስሜታዊ እና/ወይም አካላዊ) የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ተማሪን ከትምህርት ገበታ፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ከሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ ለምሳ ወይም ለእረፍት እንዳይወጣ/እንዳትወጣ ለማግለል ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

C. አካል ጉዳተኛ ተማሪ በማስተማር ላይ እና በሌሎች ፕሮግራሞች ውስጥ ለመካተት ተግዳሮቶችን የሚፈጥር ሁኔታ ካጋጠመ፣ አግባብነት ያለው የት/ቤት ቡድን ተማሪው(ዋ)ን እንደ ሌሎች ተማሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለማካተት ምን አዲስ ወይም ተጨማሪ ዘዴና ስልት እንደሚያስፈልግ ለመወሰን IEP ስብሰባ የመጥራት ሃላፊነት አለባቸው።

D. ተማሪ የሚገለልበት ሥፍራ –

1. የትምህርት ቤት ሠራተኞች ሁልጊዜም ተማሪን ለማየት በሚያስችላቸው ቦታ፣

2. በቂ ብርሃን የሚገባበት፣ በቂ አየር ያለበት፣ እና በአስፈላጊ ሁኔታ የተሰናዳ ቦታ፣ እና

3. ወጥቶ እንዳይሄድ ለመከላከል ያልታጠረ እና አደናቃፊ ነገር የሌለበት ቦታ መሆን አለበት።

E. የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለብቻ እንዲቆይ የተደረገ(ች)ውን ተማሪ ለመከታተል ሁኔታው የሚያመች እንዲሆን እና የተገለለ(ች)በትን ምክንያት ለተማሪው(ዋ) ማስረዳት አለባቸው –

1. ለብቻ ተገልሎ/ተገልላ እንዲቆይ/እንድትቆይ የተደረገ(ች)በትን አስቸጋሪ ባህርይ ማስረዳት፣ እና

2. ወደ ትምህርት ለመመለስ የሚያስፈልገውን አይነት ባህርይ ማስረዳት።

F. የትምህርት ቤት ሠራተኞች እያንዳንዱን ለብቻው(ዋ) እንዲቆይ/እንድትቆይ የማግለል ጊዜ --- መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው

1. ከተማሪው(ዋ) የእድገት ደረጃ እና ከአስቸጋሪ ባህርይ ሁኔታ ጋር የሚመጥን ተገቢነት ያለው መሆኑን፣ እና

2. ከግማሽ ሠዓት (30) ደቂቃ መግለጥ የለበትም።

G. የተማሪ ባህሪ የማስተማር መርሃግብሩን በጣም የሚያውክ፣ እና የሌሎች ተማሪዎችን ትምህርት የመከታተል ሁኔታ የሚጎዳ ከሆነ፣የክፍል መምህሩ ለጊዜው ተማሪው(ዋ)ን ከክፍል አስወጥቶ(ታ) ተማሪው(ዋ)ን ወደ ርእሰ መምህር/ተወካይ በማስተላለፍ ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይችላል/ትችላለች። ይህም፦ ISI፣ ISS፣ ከትምህርት ቤት ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፣ ወይም ሌላ አማራጭ የቅጣት ርምጃ ሊሆን ይችላል። መምህሩ(ሯ) ከአስተዳዳሪው/ከተወካዩ ጋር የመነጋገር እድል እስኪያገኝ ድረስ ተማሪው(ዋ) እንደገና ወደዚያ ክፍል እንዳይገባ/እንዳትገባ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች። እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ አለበት። ወደ መማርያ ክፍል ከመመለሱ(ሷ) በፊት፣ ርእሰመምህሩ(ሯ)/ተወካይ መፍትሄ ላይ የመድረስ ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።

1. ከክፍል መምህር ጋር ከተነጋገረ(ች) በኋላ ርእሰ መምህሩ/ተወካይ በችግሩ ላይ ለመወያየት እና መፍትሄ ለመፈለግ ስብሰባ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ከታመነ በተቻለ ፍጥነት የስብሰባ ጊዜ ያደራጃል፤ ይህም ርእሰመምህሩን/ተወካይ፣ መምህሩን እና ተገቢነት ያላቸው ልዩ ባለሙያዎችን ያጠቃልላል።

2. በዚህ ኮንፈረንስ ወቅት ሁሉንም የሚያረኩ እርምጃዎች ካልተገኙ፣ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ፣ ከክፍል አስተማሪው ጋር ከተማከሩ በኋላ፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ (ከትምህርት ቤት) አግባብነት ያለው ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ ተወካይ፣(OSSWB) እና/ወይም ደህንነት፣ መማር እና ስኬት ቢሮ ጭምር የሚገኙበት ሌላ ኮንፈረንስ መጥራት ይቻላል።

3. ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ፣ ከመምህሩ ጋር ከተማከሩ በኋላ፣ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተማሪው(ዋ) በምን ያህል ጊዜ ወደ ክፍል እንደሚመለስ ይወስናል።

H. ወላጆች/ሞግዚቶች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች በማንኛውም ጊዜ ስለማግለል እና ውሳኔ ስለመስጠት ስብሰባ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ –

1. FBA መተግበር፣ እና

2. የተማሪን BIP ለማዘጋጀት፣ ለመገምገም፣ ወይም ክለሳ ለማድረግ።

I. የትምህርት ቤት ሠራተኞችም –

1. የአካል ጉዳተኛ ያልሆነ(ች) ተማሪ ብዙ ጊዜ ወይም ተደጋጋሚ ጊዜ የማግለል ርምጃ ከተወሰደ (ለምሳሌ፦ እያንዳንዱ የመገለል ጊዜ ከ 5 ደቂቃ በላይ ሆኖ በሳምንት ከአምስት ጊዜ በላይ ከተደረገ) በሜሪላንድ ህግ መሰረት ተማሪው(ዋ) የልዩ ትምህርት ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት አካል ጉዳተኛ መሆኑ(ኗ)ን ለመወሰን፤ ወደ ትምህርት አስተዳደር ቡድን (EMT) ወይም IEP ቡድን የማስተላለፍ አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው።

2. የአካል ስንክልና ያለበ(ባ)ትን ተማሪ ምደባ መቀየር ሊያስከትል የሚችል ለበርካታ ጊዜ ተደጋጋሚ የመገለል ሁኔታ ደርሶበ(ባ)ት እንደሆነ በሜሪላንድ ህግ መሠረት ተገቢ የሆነ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

J. በተደጋጋሚ የሚደረግ ከክፍል ማስወጣት/ማግለል፣ ኦንላይን ሞጁል በመጠቀም የተማሪ መረጃ ሲስተም ላይ መመዝገብ አለበት።

## VI. የአካል እንቅስቃሴን መገደብ/ማገጃ

A. የአደጋ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ እና አካላዊ እንቅስቃሴን መገደብ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲታቀብ ማድረግ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተከለከለ ነው ወይም ተገቢ እንደማይሆን ተደንግጓል። ጉዳዩ ምንም ይሁን ወላጅ/አሳዳጊ በተማሪው BIP ወይም IEP ላይ አካላዊ እገዳን ለማካተት የጽሁፍ ፍቃድ ቢሰጡም ወይም የጽሁፍ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ባይሆኑም ማለት ነው።

1. በራስ ወይም በሌሎች ላይ የሚደርስ ከባድ የአካል ጉዳት አደጋ እንደማይከሰት ከተረጋገጠ አካል ማቀብ/እገዳው ይቋረጣል።

2. በሜሪላንድ ህግ ላይ እንደተደነገገው የአካል ማገጃ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ወይም የት/ቤት ሰራተኞች የተለየ ተማሪ-ተኮር ውሳኔ መሠረት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት፣እና ድንገተኛ ሁኔታ ከተከሰተ የተማሪን ባህሪ ለማቅናት የአካል እገዳ/ማቀብ እርምጃ በተማሪው(ዋ) BIP ወይም IEP ውስጥ ሊካተት ይችላል። የትምህርት ቤት ሰራተኞች ---

a) የተማሪው(ዋ)ን የሕክምና ታሪክ ወይም የአካል ማገጃ አጠቃቀምን ያለፈ ጉዳት የደረሰ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ማንኛውንም ተቃራኒ ሁኔታ ለመለየት እንደአስፈላጊነቱ ከህክምና ወይም ከአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ጋር መማከርን ጨምሮ ያለውን መረጃ መገምገም፣

b) በአስቸኳይና ድንገተኛ ሁኔታ የአካል ማገጃ/ማቀብ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ለተማሪው(ዋ) ባህሪ ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግሉትን አካላዊ እቀባ ያልሆኑ ጣልቃ ገብነቶችን መለየት፣ እና

c) በሜሪላንድ ህግ ድንጋጌ መሠረት ከወላጅ/ሞግዚት በጽሑፍ የስምምነት ማረጋገጫ ማግኘት።

B. የአካል ማገጃን መጠቀም

1. የአካል ማገጃ መደረግ ያለበት በአግባቡ ስለመጠቀም ስልጠና በተሰጣቸውና ለዚህ ተግባር በተመደቡ የትምህርት ቤት ሠራተኞች አማካይነት ብቻ ነው።

2. የአካል ማገጃ ጥቅም ላይ የሚውልበት እያንዳንዱ ሁኔታ የአጠቃቀሙን ተገቢነት እና የተማሪው(ዋ)ን፣ የሌሎች ተማሪዎችን፣ የመምህራንን እና የሌሎች ሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ በጥንቃቄ፣ ያለማቋረጥ ለማየት እና ክትትል ለማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ሊሆን ይገባል።

3. የአካል ማገጃን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ፣ የት/ቤት ሰራተኞች ተማሪን ወይም ሌላ ሰውን ሊደርስ ከሚችል ከባድ የአካል ጉዳት ለመጠበቅ እንደ አስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ ኃይል ብቻ መጠቀም አለባቸው።

4. የአካል ማገጃው/ማቀብ –

   a) ተማሪው(ዋ) እንደተረጋጋ(ች) ወዲያውኑ መወገድ አለበት፣ እና

   b) ከግማሽ ሠዓት (30 ደቂቃ) መብለጥ የለበትም።

5. አካልን ለማገድ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ማድረግ የሌለባቸው –

   a) የተማሪን ፊት ወደ ታች ወለል በማዘቅዘቅ የሚደረግ የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ መጠቀም፣

   b) የተማሪን ፊት-ወደታች በማዘቅዘቅ ማስቀመጥ ወይም የተማሪን የአየር መተላለፊያ መተንፈሻ አካል የሚያደናቅፍ ወይም የተማሪን የመተንፈስ አቅም የሚጎዳ፣ ሰራተኛው የተማሪውን ፊት ለማየት እንዳይችል የሚያደናቅፍ፣ተማሪን የሚያስጨንቅ የተማሪን ጭንቅላት፣አንገት፣ ወይም አካል፣ የማንቀሳቀስ ችሎታን የሚገድብ ወይም ጫና በሚፈጥር ሁኔታ ማቀብ፣ ወይም

   c) የተማሪን አካል አንፈራጦ መዘርጋት።

2. ከአካል እንቅስቃሴ እቀባ በኋላ ---

   a) በእንቅስቃሴ ማገጃ ምክንያት አካላዊ ጉዳቶች ወይም ጭንቀት ደርሶበ(ባ)ት እንደሆነ ለማወቅ ተማሪው(ዋ) በጤና ክፍል ሰራተኛ ምርመራ ይደረግለ(ላ)ታል፣

   b) ማናቸውም ቅሬታዎች ይመዘገባሉ፣ እና

   c) በተማሪው(ዋ) BIP ወይም IEP ላይ የተገለፀ ካልሆነ በስተቀር የተማሪው(ዋ) ወላጆች/ሞግዚቶች 24 ሠዓት ጊዜ ውስጥ እንዲያውቁ መደረግ አለበት።

C. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቱ ሠርተፊኬት ከሌለው እና የጋራ ኮሚሽኑን መስፈርቶች የማያሟላ ከሆነ መካኒካል የአካል እንቅስቃሴ ማገጃ መጠቀም የተከለከለ ነው።

1. በየትኛውም ሠርተፊኬት ያለው ትምህርት ቤት፣ ሁሉም ሂደቶች ቢጋራ ኮሚሽን ደንቦች መሰረት መተግበር አለባቸው።

VII. **ማግለል፣ ለብቻው(ዋ) ተነጥሎ(ላ) እንዲቆይ ወይም እንድትቆይ ማድረግ**

በማንኛውም የሜሪላንድ ህዝባዊ ኤጀንሲ ውስጥ የማግለል ሁኔታን መጠቀም በሜሪላንድ ህግ የተከለከለ ነው።

A. በሜሪላንድ የተብራራ ህግ/ደንብ፣ የትምህርት አንቀፅ 7-1102 መሰረት ህዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ማግለል ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ህዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት ሲያስገባ፣ MCPS የተማሪዎቹን መነጠል/መገለል ለመፈተሽ እና/ወይም ለመከታተል የሜሪላንድን መስፈርቶች ይከተላል።

VIII. **እንቅስቃሴን መገደብ እና ማግለልን ስለመመዝገብ**

A. ሪፖርት የማድረግ መስፈርት

1. አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት አመት 10 ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ የአካል እንቅስቃሴው(ዋ) እንዲታቀብ ከተደረገ፣ የተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ዳይሬክተር/ተወካይ ማሳወቅ አለበት፣ እሱም ሳይዘገይ MSDE ማሳወቅ ይኖርበታል።

2. MCPS የሕዝብ ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ የገባ(ች) ተማሪ የአካል እንቅስቃሴ እንዲታቀብ ከተደረገ ወይም በትምህርት አመቱ ውስጥ 10 ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ለብቻ ተነጥሎ(ላ) እንዲቀመጥ/እንድትቀመጥ ተደርጎ ከሆነ፣የሕዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ለ MSDE እና ለ MCPS በፍጥነት ማሳወቅ አለበት።

3. የልዩ ትምህርት አገልግሎት ዲሬክተር/ተወካይ 10 ጊዜ ያህል ተማሪ ከአካላዊ እንቅስቃሴ እንዲታገድ ከተደረገ እና የልዩ ትምህርት ቤት የተማሪ አካላዊ እንቅስቃሴ መታቀብን የሚገልጽ ማሳወቂያ ሲደርሰው –

   a) የሕዝብ ባልሆነ ትምህርት ቤት የእያንዳንዱን የአካል እንቅስቃሴ መታቀብ ወይም የመገለል ሁኔታን ጨምሮ የተማሪን ጉዳይ መገምገም፤

   b) ባነሰ ደረጃ የአካል ማወራጨትን ማቀብ ይቻል እንደሆን ለመገምገም የባህሪ-ጤንነት ጣልቃገብነት የህዝብ ት/ቤትን ወይም የህዝብ ያልሆነ ት/ቤትን የስነምግባር-ጤና ጣልቃገብነት አሰራር መገምገም፤ እና

   c) የአካል ማወራጨት እገዳዎችን በተመለከተ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ምክረሃሳቦችን ከ MSDE እና ከተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት ወይም የሕዝብ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ጋር ማጋራት።

B. በተማሪ ሪከርድ ላይ የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን መሰነድ

1. ተማሪ በአካል ማወራጨት እገዳ ውስጥ በገባ(ች) ቁጥር፣ የተሳተፉት የት/ቤት ሰራተኞች በተሰየመው የኦንላይን ሞጁል ላይ የሚከተለውን መረጃ መግለጫ መመዝገብ አለባቸው፡-

a) ሌላ ያልተሳኩ ወይም አግባብ ያለመሆናቸው የተረጋገጠ ቀለል ያሉ ጣልቃገብ እርምጃዎች

b) ድንገተኛ/በችኮላ ክስተት ወዲያውኑ የአካል መወራጨት እገዳ አጠቃቀምን ያነሳሳውን ባህሪ ድርጊት መግለፅ

c) የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን ያነሳሳው ባህሪ

d) የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን ያነሳሳውን ባህሪ የተመለከቱ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ስም

e) የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን የሚተገብሩ እና የሚቆጣጠሩት የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ስም እና ፊርማ

2. ሰነዱ የእቀባውን ክስተት መግለጫ ጨምሮ –

a) የአካል ማወራጨት እንቅስቃሴ እገዳው ዓይነት፣

b) የእገዳው ጊዜ ርዝመት፣

c) በእገዳው ወቅት የተማሪው(ዋ) ባህሪ እና አፀፋ/ምላሽ፣ እና

d) ስለ አካላዊ እንቅስቃሴ ማገድ ተግባራዊ መደረጉን የተገለፀለት አስተዳዳሪ ስም እና ፊርማ።

C. በዚህ ክፍል የተገለጹት ሰነዶች በተማሪው(ዋ) የትምህርት መዝገብ ውስጥ እንዲቀመጡ እና በሜሪላንድ ህግ እና MCPS ደንብ JOA-RA፣የተማሪ ሪከርድ መሰረት የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ እንዲመለከቱት ተደራሽ መሆን አለበት።

D. እገዳ በተጠቀሙ ቁጥር ወላጆች/አሳዳጊዎች በተማሪው(ዋ) BIP ወይም IEP ውስጥ ካልተካተተ በቀር 24 ሰአት ውስጥ የቃል ወይም የጽሁፍ ማሳወቂያ ሊሰጣቸው ይገባል።

E. የሚመለከተውን ተማሪ የአካል ማወናጨፍ እገዳ መጠቀም ከህክምናው ጋር የማይቃረን መሆኑን የሚያረጋግጥ የህክምና ሰነድ መኖር አለበት። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ስለሚቃረንበት ሁኔታ ሠራተኞች በግል የጤና ባለሙያዎች ጋር እንዲያነጋግሩ ወላጆች/አሳዳጊዎች ፈቃዳቸውን በፊርማ እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ። እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲከሰት ለአካል ማወራጨት እንቅስቃሴ ማገጃ ኣማራጮች ኣገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያስፈልጋል።

## IX. የአካል እንቅስቃሴ እገዳ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ወደ ... ስለማስተላለፍ

A. በአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ ወይም 1973 የመልሶ ማቋቋም ህግ አንቀጽ 504 በአካል ጉዳተኛነት ላልተሰየመ(ች) ተማሪ የአካል ማወራጨት እገዳው ከተተገበረ ወዲያውኑ ወደ EMT፣ ለትምህርት ቤት የሴክሽን 504 ቡድን፣ ወይም IEP ቡድን፣እንደአግባቡ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። ስብሰባው የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን ያነሳሳውን ባህሪ ዋናውን መንስኤ እና ስለ አጣዳፊው ክስተት ውይይት ማካተት አለበት።

B. የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ተማሪዎች፣ የተማሪው(ዋ) IEP ወይም BIP የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን ካላካተተ፣ ት/ቤቱ ጉዳዩ በተከሰተ 10 የስራ ቀናት ውስጥ IEP ስብሰባ ለማድረግ ቀጠሮ ይይዛል።

1. FBA አስፈላጊነት፣

2. አግባብነት ያለው የተማሪ ባህርይ ማቅናት ጣልቃገብነት መርኃግብር መዘጋጀት ይኖርበት ይሆናል፣ እና

3. BIP ተግባራዊ ማድረግ።

4. ስብሰባው የአደገኛ ባህሪውን ዋና መንስኤ ወይም ዓላማ ውይይት ላይ ማካተት አለበት።

5. ከዚህ በታች በክፍል XIII.F ላይ እንደተገለጸው በተማሪው(ዋ) IEP ወይም BIP ውስጥ የአካል መገደብን ለማካተት የወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ያስፈልጋል።

C. የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ተማሪዎች፣ የተማሪው(ዋ) IEP ወይም BIP ከወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ ጋር የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን የሚያካትት ከሆነ፣ ይህን አይነት አገልግሎት በሚመለከት የሜሪላንድ ህግ መሠረት፥ የተማሪው(ዋ) IEP ወይም BIP ቡድን ለመገምገም ወይም ከለሳ ለማድረግ በምን ያህል ጊዜ እንደሚሰበሰብ ይገልፃል። IEP ቡድን የተማሪን IEP ወይም BIP ለመገምገም ስብሰባ በሚያደርግበት ወቅት፣ ሒደቱ፣ አሠራሩ ስለ ስፔሻል ኢጁኬሽን የፌደራል እና የስቴ ህጎችን ድንጋጌ መከተል ይኖርበታል፣ እና IEP ቡድን ግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት---

1. በህክምናው ሁኔታ ወይም ያለፈ ዘግናኛ ገጠመኝ ያስከተለው ጉዳት ላይ በመመርኮዝ የአካል እገዳ አጠቃቀምን የሚፃረር ማናቸውንም ሁኔታዎች ጨምሮ የጤንነት ሁኔታ፣ አካላዊ፣ ሳይኮሎጂያዊ እና ስነ-ልቦናዊ መረጃ፣

2. ከወላጅ/ከሞግዚት የተሰጠ መረጃ፣

3. በመምህራን እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጭዎች የተስተዋሉ ነገሮች፣

4. የተማሪው(ዋ) የወቅቱ ምደባ፣ እና

5. IEP ቡድን ለመጨረሻ ጊዜ ከተገናኘ በኋላ የተከሰቱት የአካል እገዳ ድግግሞሽ እና የቆየበት ያህል ጊዜ።

D. IEP ቡድን የአካል እገዳ አጠቃቀምን የሚያካትት የተማሪው(ዋ)ን IEP ወይም BIP ሲቀይር በሜሪላንድ ህግ መሰረት MCPS ለወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ይሰጣል።

E. የወላጅ/አሳዳጊ ስምምነት

1. ቡድኑ የተማሪን ባህሪ ለማቅናት BIP ወይም IEP ውስጥ የአካል እገዳን ለማካተት ሀሳብ ካቀረበ IEP ቡድኑ የወላጅ/የአሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

2. ወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፍቃድ ካልሰጡ፣ IEP ቡድኑ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለወላጅ/ለአሳዳጊ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ይልካል –

a) ወላጅ/አሳዳጊ የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀምን የመስማማት ወይም የመቃወም መብት አላቸው፣ እና

b) ወላጅ/አሳዳጊ 15 የስራ ቀናት ውስጥ IEP ቡድን ስብሰባ ላይ ይሁንታ ወይም እምቢታ ካልሰጡ፣IEP ቡድን የታሰበውን የአካል ማወራጨት እገዳ አጠቃቀም ሊተገበር ይችላል።

3. ወላጅ/አሳዳጊ አለመስማማታቸውን በጽሁፍ ከሰጡ፣ IEP ቡድን ለጉዳዩ መፍትሔ ለማግኘት በሜሪላንድ ህግ የተደነገገውን የክርክር-መፍትሄ አማራጮችን ሊጠቀም ይችላል።

## X. ልዩ ሁኔታዎች እና የተከለከሉ ድርጊቶች

A. በመስተጋብር ወቅት በተማሪው(ዋ) በኩል የሚታየው የባህርይ ሁኔታ ማስፈራራት ካለው (ማለትም፡- የአካል ጉዳት የማድረስ ሁኔታ)፣ MCPS ደንብ COA-RA መሠረት ሠራተኞች የባህሪይ ስጋቶችን የመመርመር ሂደት መጀመር አለባቸው /የሚያሰጋ ባህርይን መፈተሽ።

B. በተወሰኑ ሁኔታዎች የመከላከያ ወይም የማረጋጊያ መገልገያዎችን መጠቀም፥ ተግባራዊ ክህሎትን ለማጎልበት፣ ራስን የመጉዳት ባህሪን ለመከላከል እና/ወይም የአንድን ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ አቀማመጥ ለማረጋገጥ ይፈቀዳል።ሰራተኞቹ የመከላከያ ወይም የማረጋጊያ መገልገያ መጠቀም የሚችሉት በጤና ባለሙያ በተፈቀደው መሰረት ወይም ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተማሪው(ዋ) IEP ወይም BIP መሰረት ነው።

C. ትምህርት ቤቶች ባህሪን ለመቆጣጠር ወይም የአካል ማወራጨት ነፃነትን ለመገደብ (ፈቃድ ካለው ሀኪም ወይም ሌላ ብቁ የጤና ባለሙያ ካልተፈቀደለ/ላት በስተቀር) በጭራሽ መድሃኒት መጠቀም የለባቸውም።

D. የአካል ማወራጨት እገዳን በፍፁም እንደ ቅጣት ወይም ዲስፕሊን፣ ለማስገደድ፣ ወይም የበቀል ዘዴ፣ ወይም ምቾት ለመፍጠር ታስቦ ተግባራዊ መደረግ የለበትም።

E. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በማንኛውም ሁኔታ የአካል ቅጣት የተከለከለ ነው።

## XI. ሙያ ማዳበር/የሙያ እድገት

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለትምህርት ቤት ሠራተኞች ስለዚህ ደንብ ተገቢ አፈጻጸም በሚመለከታቸው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች አማካይነት የሙያ ስልጠና ይሰጣል።

1. እያንዳንዱ የሰለጠነ የት/ቤት ሰራተኛ በአመት የማሻሻያ ኮርስ መውሰድ ይጠበቅበታል።

2. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ድንገተኛ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት የአካል ማወራጨትን ማገጃ ተግባራዊ ለማድረግ ቢያንስ አምስት የሰለጠኑ አባላት ያሉት የቀውስ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ቡድን ሊኖረው ይገባል።

B. ስልጠናው በተገለጹት ክህሎቶች እና ብቃትን ለመፈተሽ የጽሑፍ ፈተና እና/ወይም የአካል ሰርቶ ማሳያ ብቃትን ያካትታል፣ እናም –

1. እንዳይባባስ ለማድረግ እና አወንታዊ የተማሪ ባህሪ የማቅናት ጣልቃ ገብነት ስልቶች/ስትራቴጂዎች እና ድጋፎች፣ አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ባህሪያትን መለየት እና መቆጣጠር መቻልን ጨምሮ፤

2. በአሰቃቂ ሁኔታ ገጠመኝ ምክንያት የሚከሰት የባህሪ ሁኔታን የመቆጣጠር ጣልቃ ገብነት፣

3. FBA እና BIP እቅድ እና ሂደቶች፤

4. ማግለል፣

5. የአካል ማወራጨት እንቅስቃሴ እገዳ እና ሌሎች አማራጮች፣

6. በሁሉም የሜሪላንድ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የማግለል መከልከል፣

7. አካላዊ ጭንቀት እና በአቀማመጥ ሁኔታ መታፈን ወይም መተንፈስ ያለመቻል ምልክቶች፣

8. የትንፋሽ እጥረት እና ከልብ ጋር የተያያዘ የመጀመሪያ እርዳታ (CPR)፣

9. አካል ጉዳተኝነትን፣ የህክምና ሁኔታ፣ እና ያለፈ አሰቃቂ ገጠመኝ ያስከተለ ጉዳትን ጭምር በተማሪ ባህሪ ላይ በሚታዩ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ግለሰባዊ የባህሪ ማቅናት ጣልቃገብነት፣ እና

10. ራስን የሚጎዳ-የሚያቆስል አይነት ባህርይን መከላከል

## XII. ለተማሪዎች እና ለወላጆች/ለሞግዚቶች መሰጠት ያለበት መረጃ

A. የዚህ ደንብ ማስታወቂያ በሚመለከተው አካል እየታተመ በየዓመቱ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሠራጫል።

B. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ እንዲደረግ ሊጠይቁ ይችላሉ።

1. FBA ለመተግበር፤

2. የተማሪን BIP ለማዘጋጀት፣ለመገምገም ወይም ለመከለስ፤ እና/ወይም

3. ኣለዚያም ስለተማሪው(ዋ) ለመወያየት።

## XIII. ተግባራዊ ማድረግ፣ቁጥጥር፣ እና ግምገማ

A. ርእሰ መምህሩ(ሯ) በትምህርት ቤት መተግበር ያለባቸው አሠራሮችን የማካተት ሃላፊነት አለበ(ባ)ት –

1. በእያንዳንዱ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ፡- የሙያ ማዳበር ስልጠና የሚያገኙ እና የዚህ ደንብ ትክክለኛ አተገባበርን ለማረጋገጥ የሚረዱ የትምህርት ቤት ግብረኃይል ሆነው የሚያገለግሉ ሰራተኞችን ያቀፈ አምስት አባላት ያሉት የቀውስ ክስተት ተቆጣጣሪ ቡድን መለየት፣

2. የእገዳ ሂደቱ ተማሪን ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ክፍለጊዜ ማግለል በጊዜያዊነት ከትምህርት ቤት የማገድ ሂደትን ካልተከተለ በስተቀር ከትምህርት ቤት መታገድን የማይጨምር መሆኑን ማረጋገጥ፤

3. አካላዊ ቅጣት፣ያለውን/ያላትን ሥልጣን በመጠቀም ሆን ተብሎ የሚደረግ የአካል ቅጣት መሆኑን ለትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ማሳወቅ —

a) የተከለከለ፣

b) MCPS ደንብ JHC-RA መሠረት፣ የህጻናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ እና

c) ሠራተኛው(ዋ) የዲሲፕሊን እርምጃ የወሰደ(ች)በት ምክንያት(ቶች)።

4. የማግለል እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ማሳወቅ –

a) የተከለከለ፣

b) MCPS ደንብ JHC-RA መሠረት፣ የህጻናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ እና

c) ሠራተኛው(ዋ) የዲሲፕሊን እርምጃ የወሰደ(ች)በት ምክንያት(ቶች)።

5. አካላዊ ቅጣት ወይም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ድርጊት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ የተፈፀመ ከሆነ ሁኔታውን ለሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ እና OSSWB ለሚመለከተው ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ማሳወቅ፣

6. በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ የአካል ማገጃ የተጠቀሙ መሆኑን ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ እና ክስተቱ በተፈጠረ 24 ሰአት ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ መግለጽ፣

7. እያንዳንዱ የአካላዊ እገዳ ክስተት በትምህርት ሪከርዱ ላይ ሰነድ መያዙን ማረጋገጥ፣

8. እያንዳንዱን የአካላዊ እገዳ ክስተት ለዚህ ተግባር በተመደበው የኦንላይን ሞጁል ላይ መመዝገብ፣

9. Office of Human Resources and Development/Department of Compliance and Investigation and the Office of Special Education (OSE) ጋር በመመካከር የማግለል እና የመገደብ ተሞክሮዎችን በሚመለከት ቅሬታዎችን መቀበል እና መመርመር

10. የሠለጠኑ ሠራተኞች ብቻ እገዳን ማከናወን እንደሚችሉ ለሠራተኞች ማሳወቅ።

B. በዚህ ደንብ እና በሜሪላንድ ህግ መሰረት MCPS የአካል እገዳ አጠቃቀምን ይቆጣጠራል።

C. ማግለል ወይም የአካል ማወራጨትን ማቀብ (ወይም IEP ምደባ መሰረት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ በተመደበ(ች)በት ህዝባዊ ያልሆነ ትምህርት ቤት በአንድ ቦታ ብቻው(ዋ)ን እንዲሆን/እንድትሆን ማግለል) በአንድ ተማሪ ላይ በተደጋጋሚ ተግባራዊ ከተደረገ፣ በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ ከተደረገ ወይም አብዛኛውን ጊዜ በተመሳሳይ ግለሰብ የተፈፀመ ከሆነ፣ የበለጠ ጥልቅ ግምገማ ይካሄዳል፤ እና አስፈላጊ ከሆነ በወቅቱ በሥራ ላይ ያሉትን የባህሪ ማቅናት ስልቶች ላይ ማሻሻያ ይደረጋል።

D. በሜሪላንድ ህግ መሠረት የዚህ ደንብ አፈጻፀም በየዓመቱ ይገመገማል።

**ተዛማጅ ግብአቶች፡-**

Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) 20 U.S.C. §1400 et seq.1990 አሜሪካውያን የአካል ጉዳተኞች ሕግ (ADA)፣ 2008 አሜሪካውያን የአካል ጉዳተኞች ማሻሻያ ህግ (ADAAA)፣ 1973 የተኃድሶ ማቋቋሚያ ህግ አንቀጽ 504፤ ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣አካላዊ እገዳ እና ማግለል የመረጃ ሰነድ (2012)፤ ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ውድ የሥራ ባልደረባዬ ደብዳቤ፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አካልዊ እገዳ እና ማግለል (ዲሰምበር 28 2016)፣ ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣ ነባራዊ እውነታ፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካል መገደብ እና ማግለል (ዲሰምበር 2016)፣ የተብራራ የሜሪላንድ ሕግ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ §§ 7-307፣ 7-1101፣ 7-1104፣ 7-1106 እና 8-405፤ 2022 የሜሪላንድ ህጎች ምዕራፍ 31 (H.B. 1255)፣ የሜሪላንድ ሕግ ኮድ (COMAR)

13A.08.01.11፣ 13A.08.01.17፣ እና 13A.08.04.02-.06፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) መመሪያ፣ COMAR 13A.08.04–የተማሪን ባህሪ ለማቅናት የሚደረጉ ጣልቃገብነቶች (ጁላይ 22 2019፣ MSDE የቴክኒክ ድጋፍ መግለጫ መፅሔት 19-02፣ የተማሪን ባህሪ ለማቅናት የሚደረጉ ጣልቃገብነቶች እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ላይ የሚደረግ የአካል እገዳ (ጁላይ 2019)፤ MCPS የተማሪዎች የስነምግባር መመሪያ ፣MCPS የሰራተኞች የስነምግባር ህግ

**የዚህ ደንብ ታሪክ፦** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 550-1፣ ኦገስት 10, 1976 (ማውጫው ተሻሽሏል)፣ ኦክቶበር 1986 ተሻሽሏል። ሰፕተምበር 10, 2004 ተሻሽሏል፣ ማርች 13, 2012 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 4, 2017 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 8, 2019 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 26, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024